# የኢትዮጵያ ህዝብ ተስፋ መቁረጥ የለበትም!

ስዬ አብርሃ ከአዲስ አድማስ ጋዜጣ

ብዕለተ ቅዳሜ ሐምሌ ሰባት ቀን 1999 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማችን ውስጥ የብዙኃኑን የልብ ትርታ ያደመጠውና በመላው ሕብረተሰብ ዘንድ መነጋገሪያ ርእስ ሆኖ የዋለው የአቶ ስዬ አብርሃ የአዲስ አድማስ ጋዜጣ ቃለመጠይቅ እንዳለ አቅርበነዋል ተቋደሱ፡፡ በነገራችን ላይ በብዙ ሽ ቅጂ የሚታተመው የዕለተ ቅዳሜ የአዲስ አድማስ ጋዜጣ በጥዋቱ ተሸጦ በማለቁ በርካታ ሕዝብ በተለያዩ ቦታዎች ጋዜጣውን ሲያፈላልግ አጥቶ እንደዋለ ታዝበናል፡፡

የአራት ኪሎው ታዛቢ

<u>ከአዲስ አበባ</u>

ከ6 አመት በፊት በኢህአዴግ ውስጥ ክፍፍል ከተፈጠረ በኋላ በሙስና ተከስሰው የታሰሩት አቶ ስዬ አብርሃ ሰሞኑን ተፈትተዋል፡፡ በኢህአዴግ የመጀመሪያ አመታት የመከላከያ ሚኒስቴር ሆነው የሰሩት አቶ ስዬ፣ ሰሞኑን ጠቅላይ ፍ/ቤት 5 አመት እስር ከወሰነባቸው በኋላ ነው እስካሁን በእስር ያሳለፉት ታስቦ የተፈቱት፡፡ የፈፀምኩት ወንጀል የለም የሚሉት አቶ ስዬ፣ መልስ ለመስጠት ፍቃደኛ በሆኑባቸው አምስት ጥያቄዎች ላይ ብቻ የሰጡንን ቃለምልልስ አቅርበናል፡፡

አዲስ አድማስ፡- ስድስት ዓመት ታስረው አምስት ዓመት ሲፈረድብዎት ምን ተሰማዎት?

አቶ ስዬ፡- አንደኛ ነገር እኔ ከመጀመሪያው ጀምሮ ንፁህ ነኝ፡፡ ያጠፋሁት ወንጀል እንደሌለ አውቃለሁ፡፡ እኔ የፍርድ ቤቱን ስርአት አክብሬ ነው ክርክሩን ለመቀጠል የወሰንኩት፡፡ ይህን ያደረግኩበት ምክንያት ፍትህ አገኛለሁ ብዬ አልነበረም፡፡ ቢያንስ ግን ስርአቱን አክብሬ በመከራከር ለታሪክ፣ ለሬከርድ፣ ለሚቀጥለው ትውልድ ይቆያል፣ የሚቀጥለው ትውልድ ይማርበታል ብዬ ነው ወደ ክርክሩ ሂደት የገባሁት፡፡ ተከላከል ሲሉኝም መከላከያ ማስረጃ አቅርቤ የተከራከርኩት በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ለዳኞቹም ከመጀመሪያ ጀምሬ ይህን ነግሬያቸዋለሁ፡፡ ፍትህ አለ ብዬ ሳይሆን የኔ ልጆች እና የእናንተ ልጆች እንዲያውቁት፣ ወደፊት እንዲማሩበት ለሪከረድ ያህል ነው ስርአቱን አክብብሬ እከራከራለሁ ያልኩት፡፡

አዲስ አድማስ፡- እፈታለሁ ብለው አስበው ነበር?

አቶ ስዬ፡- አንድ ቀን እንደምፈታ አውቃለሁ፡፡ ዳኞቹ በመጨረሻ ነገሩን እንዴት ይቋጩታል የሚለው ግን የሚያስጨንቀኝ ነገር አልነበረም፡፡ አሁን ተፈትቻለሁ፡፡ ስድስት አመት ሙሉ ግን ታስሬያለሁ፡፡ አምስት የአንድ ቤተሰብ አባላት በ13 የወንጀል ክስ እያንዳንዱ እስከ 15 ዓመት የሚያስቀጣ ክስ ተመስርቶብን ታስረናል፡፡ ይሄ ሁሉ መከራ አልፎ ለቤተሰብ፣ ለአገርና ለነፃነት መብቃቴ ደስ ይለኛል፡፡ በደል ደርሷል፣ በኔና በቤተሰቤ ላይ በደል ተፈፅሟል፡፡ ግን እኔና ቤተሰቤ በደህና እስከወጣን ድረስ ወደኋላ መመለስ

አልፈልግም፡፡ በወደፊት ህይወቴን ለአገርና ለወገን በሚጠቅም ነገር ላይ እንዳተኩር ጉልበቴንም ለዛ እንዳውል እንጂ ወደኋላ እያሰብኩ በጥላቻና በቂም እራሴን፣ ጤናዬን፣ ጉልበቴንና ጊዜዬን ላባክን አልፈልግም፡፡

አዲስ አድማስ፡- ህወሐት ውስጥ መከፋፈል በተፈጠረበት ወቅት ከእርስዎ ጋር ከድርጅቱ የወጡ ሰዎች ሌላ ርቲ በመመስረት ሂደት ላይ ናቸው፡፡ ርቲውን ይቀላቀላሉ?

አቶ ስዬ፡- የፖለቲካ ፓርቲ ለኔ ትልቅ እና ከባድ ውሳኔ ነው፡፡ የትጻር ጓደኛ የመምረጥ ያክል ነው፡፡ ፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ መግባትን አክብጄ ነው የማየው፤ አጥንቼ ተጠንቅቄ የምገባበት ነገር ነው፡፡ ብዙ አላውቅም፤ ግን ጓደኞቼ ዝግጅት ያደርጉ እንደነበር ማመልከቻም እንዳስገቡ ሰምቻለሁ፡፡ ዝርዝሩን አላውቅም፡፡ ጓደኞቼን በጣም አከብራቸዋለሁ፡፡ እነሱ የሚሉትንም አዳምጣለሁ፤ ቢሆንም ግን የራሴን ጥናት አድርጌና ከራሴ ጋር መክሬ የምወስነው ነው፡፡ አሁን በዚህ ጉዳይ ላይ ይህን አደርጋለሁ ብዬ የምወስንበት ጉዳይ አይደለም፡፡

አዲስ አድማስ፡- ለኢትዮጵያ ህዝብ ምን ይላሉ?

አቶ ስዬ፡- በእርግጥ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ ችግር አሳልፏል፡፡ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ፤ ሰውን የኑሮ ምስቅልቅል ውስጥ የሚያስገባ ታሪክ ሆኗል፡፡ እዚህ አገር ያሉት ፖለቲከኞችም ለመጥፋት እንደተቃረቡ ዝርያዎች ናቸው፡፡ ያም ቢሆን ግን የአገራችን ሁኔታ በምክክር፣ በፖለቲካዊ ውይይት፣ በመቻቻል እና ለህዝብ ፍላጎት ተገዢ በመሆን ካልሆነ በስተቀር በሌላ መንገድ ሊፈታ እንደማይቻል አምናለሁ፡፡ በእርግጥ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ አይቷል፤ በፖለቲካ ምስቅልቅል ብዙ ችግር አሳልፏል፡፡ ግን ተስፋ አለመቁረጥ ተስፋን ሰንቆ፣ የአገርን ሁኔታ የተቻለውን ያህል ለማስተካከል መጣር አለብን እንጂ ችግሮች በተፈጠሩ ቁጥር ተስፋ መቁረጥ፤ አንዱ ባንዱ ላይም ተስፋ መቁረጥ ያለበት አይመስለኝም፡፡

አዲስ አድማስ፡- በአንድ ወቅት እርስዎ እንዲፈቱ ውሳኔ የሰጠችው ብርቱካን ሚደቅሳ አሁን በእስርቤት ትገኛለች፡፡ ምን ያስባሉ?

አቶ ስዬ፡- መልካም ዳኛ መሆን በኔ ግምት ሁለት ነገር የሚጠይቅ ይመስለኛል፡፡ አንደኛ የህግ እውቀት፤ ሁለተኛ የሞራል ድፍረት፡፡ ሁለቱም ከሌሉ ነፃ ዳኛ ነፃ ዳኝነት ይኖራል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ወ/ት ብርቱካንን አላውቃትም፡፡ እዛ ችሎት ብቻ ነው ያየኋት፡፡ ሁለቱንም ይዛ ያገኘኋትና ዳኛ መሆን የሚገባት ሰው ናት ብዬ አምናለሁ፡፡ እንደዚህ ያለች ዳኛ እስረኛ መሆኗ በጣም ያሳዝነኛል፡፡

የአቶ ስዬ ባለቤት ወ/ሮ ሀዳስ አለሙ

በጣም ነው ደስ ያለኝ፡፡ ከስድስት አመት በኋላ በሰላምና በጤና፤ ከቤተሰቦቹና ከልጆቹ ጋር ስለተገናኘ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ ደስታዬን መግለፅ አልችልም፡፡ አላውቀውም፡፡ አንድ ቀን ይፈታል ብዬ አስብ ነበር፡፡ ቀኑ ደረሰና ቤቱ ገባ፡፡ ብዙ ችግር ብዙ ውጣ ውረድ ነበር፡፡ ሁሉም አልፏል፡፡ በተለይ ከርቸሌ ብዙ ነገር አይቻለሁ፡፡ ሬሳ ሲወጣ አይቻለሁ፡፡ አዕምሯቸው የተበላሸ ሰዎች አይቻለሁ፡፡ በአጠቃላይ ይህ አይነት ሁኔታ ሳይገጥመው ከነሙሉ ጤንነቱ በመምጣቱ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡